# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

*2014/42*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

**የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ፤ በሶማሌ ክልል አዲስ የውሃ ስርጭት መስመሮችን ዘረጋ**

*በአጠቃላይ150,000 በላይ ዜጎች ከንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽነት መርሃ ግብር ተጠቃሚ ይሆናሉ*

***ህዳር 9፣ 2014፤ ሶማሌ ክልል፣ ኢትዮጵያ፡-*** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በሶማሌ ክልል ጉባድለይ ቀበሌ የኤጀንሲው የውሃ ፕሮጀክት አካል የሆነውና በዓለም አቀፉ ሕይወት-አድን ኮሚቴ (IRC) የተተገበረውን አዲስ የውሃ አገልግሎት መስጫ ማዕከል በዛሬው ዕለት መርቀው ከፈቱ፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኤጀንሲ በዓለም አቀፉ ሕይወት-አድን ኮሚቴ በኩል ከአካባቢው ማህበረሰብና ከባለሥልጣናት ጋር በመተባበር 2,100 የሚሆኑ የቀበሌውን ነዋሪዎች ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ በጉባድለይ ቀበሌ የተገነባው ይኸው የውሃ ማሰራጫ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ መርጫ የተገጠመለት ጥልቅ ጉድጓድ፣የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖችና እያንዳንዳቸው አራት ውሃ የሚወርድባቸው ቧንቧዎች የተገጠሙላቸው ሁለት ቦኖዎች አሉት፡፡

ዋጂ፣ ዱማሌ፣ ሳንጉማሬ፣ ታውላኔ፣ ማግላድ፣ ሂግሊለይ፣ ቡንዳዳ እና ገርጊዮን ከ52,000 በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሆኑባቸው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኤጀንሲ የውሃ ፕሮጀክት ተግባራዊ የሆኑባቸው አዲስ የውሃ ጣቢያዎች ሲሆኑ፤ ፋርዶ፣ ዶደቲ፣ ሃልጂድ፣ ሩጂስ፣ ሼኮሽ፣ ዱርዋሌ፣ ዉጂ ዋጂ፣ ዲራቶ፣ ዋጂ እል፣ ሁራሬይ አካባቢዎችም የታደሱ መሥመሮች ሲሆኑ በነዚህም 100,000 የሚጠጉ ነዋሪዎች ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኤጀንሲ እስከ ዛሬ ድረስ በውሃ ፕሮጀክቱ በሶማሌ፣ በአፋርና በኦሮሚያ ክልሎች የንጹህ ውሃ ተደራሽነትንና ዘላቂ የውሃ አቅርቦትን ለማረጋገጥ በሠራቸው ሥራዎች ከ221,000 በላይ ዜጎች ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን፤ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ መፀዳጃ ቤት መጠቀምንና ንጽሕና አጠባበቅን ከማበረታታቱም በላይ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በአካባቢ እንክብካቤ ዙሪያም የህዝቡን ንቃት ለመጨመር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኤጀንሲ የውሃ ፕሮጀክት ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ድርቅን የመቋቋም አቅም ከሚገነቡ ዋና ዋና የኤጀንሲው መርሀ ግብሮች አንዱ ነው፡፡ የኤጀንሲው ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በእነዚህ ዝናብ አጠር አካባቢዎች ውሃ ለንጽህና፣ለጤና አጠባበቅ እና በእንስሳት እርባታ ላይ ለተመሠረተው የአካባቢው ማህበረሰብ ያለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ጠቁመዋል፡፡ አክለውም፡-“የውሃ አቅርቦትን ለመኖሪያ አካባቢ ተደራሽ ማድረግ የማህበረሰቡን፤በተለይም የሴቶችን ሕይወት ከማሻሻልና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ አስተማማኝ አቅርቦት ሲኖር፤ በዚህ ውድ ሀብት ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች እንዲቀንሱም የሚያደርግ ሲሆን፤ ማህበረሰቡ በዚህ አዲሱን የውሃ አቅርቦት ዝርጋታ በማስተዳደር ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆኑ ዘላቂነቱን የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡ የአሜሪካ ሕዝብም በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ በኩል ከክልሉ መንግሥት፣ ከዓለም አቀፉ ህይወት-አድን ኮሚቴና በልማትና የንጹህ ውሃ አቅርቦትን በማረጋገጥ ህይወቱን ለመቀየር ከተነሳሳው ከዚህ ማህበረሰብ ጋር በመሥራቱ ኩራት ይሰማዋል” ብለዋል፡፡

አቶ ኤልያስ ሁሴን ከሊፍ የሶማሌ ክልል የውሃ ቢሮን በመወከል የተናገሩት ስለ ውሃ ፕሮጀክቱ አስፈላጊነት ሲናገሩ፡-“ለሶማሌ ክልል መንግሥት ከ1-5 ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ወሃ ነው፡፡ ከ9 በላይ የውሃ አቅርቦት ማዕከላትን የገነባውና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ያረጋገጠው ይኸው የውሃ ፕሮጀክት መወጣት በሚኖርብን ኃላፊነት ረገድም ትልቅ እገዛ አድርጎልናል፡፡ ክልሉ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ በቀጣይነት ተመሳሳይ ድጋፍ እንዲያገኝና ከዓለም አቀፉ ህይወት-አድን ኮሚቴ ጋርም ያለን ውጤታማ ወዳጅነት ከባልደረቦቻችን ጋር በጋራ በመሥራት እርስ በርስ የምንማማርበት እንዲሆን አላህ እንዲረዳን ፀሎቴ ነው” ነበር ያሉት፡፡

###